መጠየቅ በመሄድ ኢጅችን መሰንዘር
ይሰጥ ይሆን ብሎ ፅድልን መሞከር
ኣለማወቅ ሳይሆን ይህ ነው መደናቆር
ኣራሴን ለመጥቀም ወይ
የመጣውን ከልካይ
ኣይደለሁ «ኣኔ» ባይ...
ኣይደለማ ቅሜ ቻይ
ከርሱ ሌላ ኣላይ
ኣማትሬም ባይኔ ከሰማይ ወደላይ
ማረኝ ኣምላኬ ሆይ
ኣላለው ሰጻልይ
ጉልበት እንዲሆነኝ
በሕይወት መንገድ ላይ
ለኣምላክ ሀ ኣሏህ ሰለሌው ወደር
ከርሱ ደጅ ኣትቅር ለምነው ዘወትር
ኣምላኬ ሆይ ኣሏህ ምሰጋናዬ ሁሉ ታጅቦ በፍቅር
ብቻ ይድረሰ ላንተ ይገባሃል ክብር
ካንተ ደጅ ጠንቼ በመዋል እንዳድር
ያንተ ድሃ ሆኜ ጸንቼ እንድቀር
ጉለቤቴን ኣበርታው ደከሜያልቸገር [50]

ሸይኹል ኢስላም ተቂዩዲን ኣሕመድ ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ ተዓላ በሕይወታቸው ኣንድ ጊዜም ቢሆን ሥልጣን ፈልገው ኣያውቁም ይልቅ የሰዎችን ሁኔታ በተለይም ደግሞ በወቅቱ የእርሳቸውንና የባላንጣዎቻቸውን ተጨባጭ ስብእና ሲገልጹት ((ኣንድ ግለሠብ ሌላ ግለሠብ ዘንድ ሐቅ እንዳለ ኣያወቀ ያችን ሐቅ በድርቅና በማስተባበል ይከዳታል ። ምክኒያቱም ደግሞ ሰለተመቀኘው ኣልያም ከርሱ

በላይ ሆኖ ለመታየት ሰለሚፈልግ እና ሥልጣን ሰለሚሻ ነው ። አልያም ደግሞ ሰሜቱን የሚከተል የነፍሰያው ባሪያ የሆነ ግለሠብ ሰለሆነ ነው !!)) [51] በማለት ነው ።

ሸይኹል ኢስላም ተቂዩዲን አሕመድ ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ ግን የስልጣን ጉጉት የሚባል ነገር ያልነበራቸው ፣ አሏህ በሰጣቸው የተመጠነ ሲሳይ ተብቃቅተው በእርካታ የሚኖሩ ፣ አስፈላጊ ለሆኑ መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸው ውጭ ተጨማሪ ነገሮችን የማይሹ ፣ በአብዛኛውም ጊዜ ዳቦ በዘይት ብቻ በመመገብ ውለው የሚያድሩ ዛሂድ የሆኑ ታላቅ ሰው ናቸው ።

ሸይኽ ዘይኑዲን አልዋሲጢ ረሒመሁሏሁ ከእርሳቸው ዘንድ የተወሰኑ ወቅቶችን ኖረው ነበር ። ስለርሳቸው ሁኔታ ሲገልጹ ((*የሚመገቡት ምግብ በጣም ትንሽ ከመሆኑ የተነሳ «አባኮትን ትንሽ ይጨምሩ » ብዬ ብወተውታቸውም በዚያችው ትንሽ ምግብ ይብቃቁ ነበር ። በዚህ ሁኔታቸው አኔ ለእርሳቸው ውስጤ ይንሰፈሰፍላቸው ነበር ።*)) በማለት ነው ። [52]

አልሓፊዝ በዛር ፡ ((*ለትልቁም ለትንሹም ፣ ለባለማዕረጉም ማዕረግ ለሌለውም ፣ ቸር ለሆነው ሃብታምም ይሁን ለድሃው በሙሉ ሳያዳሉ ነበር የሚተናሱላቸው ። ቸርና ምስጉን ሥነ-ምግባር ያላቸውን ሃብታሞች እንደሚያቀርቧቸው ምስጉን ሥነ-ምግባር የተላበሱ ድሆችን ወደራሳቸው በማቅረብ አከብረው ፣ አልቀው እና ተናንሰውላቸው ቀልባቸውን የሚያስደሱ ነገሮችን በማድረግ ፣ ማራኪ ንግግሮችን በመናገር ውሰጣቸው በሃሴት እንዲበርቁ ያደርጓቸው ነበር ። አልፎም ድሃውን ሰው አራሳቸው አገልጋዩ ሆነው በመኻደም ፣ ሸክም ካለው መጓጓው ላይ ጭነውለት ፣ የሚያቀብሉት ነገርም ካለ ከተቀመጠበት አምጥተው በመሰጠት ይንከባከቡታል ። በዚህ ድርጊታቸው ቀልቡን ለመጠገንና ወደ ጌታቸው አሏህ ተበረከ ወተዓላ ውዴታ ለመቃረብ ዓልመው ነው ይህን ያደርጉ የነበረው ። ...*))[53] ሲሉ ስብእናቸውን ይገልጹታል ።

አክለውም ((*እርሳቸውን የተመለከታቸው ሰው በሙሉ ፤ በተለይም እርሳቸው ዘንድ ረዘም ላለ ወቅት ቆይቶ እንቅስቃሴዎቻቸውን ላሰተዋለ በዛሂድነት በዚህች ዓለም*

ውሰጥ አንደርሳቸው ያለ ዛሂድን ቢፈልግ ቢያፈላልግ ከቶም አንደማያገኝ ገልጾ አምሳየ አንደሌላቸው ይመሰክርላቸዋል ። የቅርቡም የሩቁም ሰለርሳቸው በትክክለኛው መንገድ ሳይበረዝ ሳይከለስ ሰብአናቸውንና ባህሪያቸውን የሰሙ በሙሉ ቀልቦቻቸው በፍቅር አትመዋቸው በታላቅ ክብር አኑረዋቸዋል ። ሌላው ቀርቶ በከተማው ውሰጥ የሚኖር ተራው ነዋሪ አንኳን አርሳቸው ዘንድ አብሯቸው ለረዥም ወቅት ሳይቆይ በጨረፍታ የሚያውቃቸው ግለሠብ " በዚህ ከተማ ውሰጥ ዓይነተኛ ዛሂድ ማን ነው ?! የዱንያን የቅምጥል ኑሮ በመተው በትንሹ በመብቃቃት የአኺራን ሕይወት ብቻ በመፈለግ አራሱን የጠመደ ሁነኛ የአሏህ ሰው ማነው?! " ተብሎ ቢጠየቅ " አንደ ሺብኑ ተይሚየህ ያለ ፈጽም አንድም ሰው አልተመለከትኩም !!" ብሎ ነው የሚመልሰው ።)) [54] ሲሉ ተናግረዋል ።

በጂሃድ ላይ የነበራቸው ገድል

ሸይኹል ኢስላም ተቂዩዲን አሕመድ ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ በሸሪዓዊ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ፈትዋ የሚሰጡ ሊቅ ብቻ አልነበሩም ፣ ኢስላማዊ መጽሐፎችንም በማዘጋጀት ብቻም አልተብቃቁም ፣ በሚልም መጅሊሶች ተማሪዎችን ሰብስበው በማስተማርም ብቻ አልተገደቡም ፣ ከማህበረሰቡም እራሳቸውን በማግለል ከማህበራዊ ሕይወት ርቀውም ከነባራዊው የሰዎች ተጨባጭ ሕይወት ሸሽተው ብቸኝነትን አልመረጡም ፣ በዙሪያቸው የሚከናወኑትን ወቅታዊ ጉዳዮች የማያውቁም ገለልተኛም ዓሊም አልነበሩም ። ይልቅ ሕይወትን ከቀልባቸው በመነጨ "በሕይወታችን ውስጥ እኔም አንድ የማህበረሰቡ አጋር ነኝ" በሚል ታላቅ ስሜትና እያንዳንዷን የሕይወት መነባብሮ ተጋፍጠው በታላቅ ጽናት ሁሉንም የሰው ዓይነት በሚማርክ ስብእና አስተናግደው ተኗኑረዋቸዋል ። ዕድሜያቸውን በሙሉ በተሰላው ብእራቸው ጂሃድ በማድረግ ፣ አንደበተ ርቱዕ በሆነው ምላሳቸው ያፈነገጡ ሰዎችን አመለካከት በማስረጃ ጸጥ ረጭ አድርጎ ፈጥጠው መውጫ ቀዳዳ እንዲያጡ አድርገዋል ። ከዚህም አልፎ ሰይፍ አንግበው በጦር አውድማ ላይ ከጀግኖችም በላይ ጀግና ሆነው ጠላትን

በመፋለም አስከንድተዋቸዋል ። የጦር ሜዳ ገድላቸውን ታሪክ አስፍሮት የተማሩትን በማስተማር እና በተግባር በማሳየት ወደር የማይገኝላቸውን እኒህን ልዩ የሆኑ ተምሳሌት አርአያ እንድንከተል በመዝገብ አኑሮታል ።

ሸይኹል ኢስላም ተቂዩዲን አሕመድ ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ የኑሩበት ዘመን በዘርፈ ብዙ ፈተናዎች የተናወጠ እና የአመለካከት ትርምሶች ከላእላይ ጉልላታቸው ላይ የወጡበት ዘመን ነበር ። ሙስሊሞች በወቅቱ ፈታኝ የሚባለውን መሪር የሕይወት ውጣውረድ ያስተናገዱበትና ጠላት ከየአግጣጫው በተለያዩ የመዝመቻ ዘዴዎች ዘምተውባቸው ቁም ስቅላቸውን ያሳዩበት የሰቆቃ ዘመን ነበር ። የመስቀላውያኑ ጦርነት እስልምናን ከምድረገጽ ለማጥፋት ጦሩን ባተመመበት በዚህ የጭንቅ ቀን ታታሮችም በፊናቸው ኢስላማዊ ግዛቶችን የራሳቸው ለማድረግ ጦራቸውን አግተልትለው አዘመቱ ። የሙስሊሞች ግዛት አንድ በአንድ በእጆቻቸው ሥር በመውቀደቅ ሙስሊሞችና ኢስላማዊ ቅርስና አልሉ የሚባሉ የምድራችን ትንግርታዊ ትውፊቶች ከምድረ ገጽ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከስመው እንዲጠፉ አገራቸውን አወዳደሙ ፣ ነዋሪዎችን እየቀሉ ገድለው የአሞራ ቀለብ አደረጓቸው ። በወረራቸውም ሙስሊም አገራትን በእጃቸው አስገብተው ወደ ማዕከላዊው መንግስት መናገሻ በግዳድ በመግባት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ደም በፈሰሰበት እና አገር በፈራረሰበት ወረራ የዓባሲዮቹን ኸሊፋ ሙዕተሲምን ገድለው ግፍ መፈጸም የቻሉበት ወቅት ነበር ።[55]

ተታሮች በሙስሊሙ ዓለም ውስጥ በእንደዚህ ዓይነት አረመኔያዊ ጭፍጨፋቸው ምክኒያት ሽብርን ሙስሊሞች ቀልብ ውስጥ መዝራት ችለው ነበር ። ይህም ሽብር ሙስሊሞች ከአገር ወደ አገር እየሸሹ ከአሰቃቂው ግድያቸው ለማምለጥ እንዲገደዱ አድርጓቸው ነበር ። በ699 ዓመተ-ሂጅሪያ የተታሮቹ መሪ ቃዛን ሻምን ለመውረው አሰቦ ነበር ። ነገር ግን ሸይኹል ኢስላም ተቂዩዲን አሕመድ ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ ከእርሱ ዘንድ በመሄድ ድርጊቱን አውግዘው በመገሰጽ ውሳኔውን እንዲሰርዝ አድርገዋል ።

በ702 ዓመተ-ሂጅሪያ ታታሮች ሻምን ለመውረር እየተሰናዱ እንደሆነ ወሬ ተሰራጨ ። ሙስሊሞች ይህ ን ወሬ ሲሰሙ በሽብር ተናወጡ ፣ ውስጣቸውም በርዕደት ተርበተበተ ፣ ልባቸው ደልቃ ጉሮሮዋቸው ስር ደርሳ የተሰነቀረች እስከሚመስላቸው ድረስ መተንፈሻ አሳጣቻቸው ። በዚህ ወቅት ሸይኹል ኢስላም ተነስተው ሕዝቡን በማረጋጋት በአላህ ቃልኪዳን እስካመኑ ድረስ በጠላቶቻቸው ላይ ባለድል እንደሚሆኑ ገስጸው በመምከር ከመረበሽና ከመሸበር ርቀው ይልቅ ለጂሃድ ሁሉም እንዲታጠቅና ዝግጁ እንዲሆን በማዘዝ ጽኑ የአሏህ ታጋዮች እንዲሆኑ ሥነ-ልቦናቸውን አድሰው ፍርሃታቸውን መግፈፍ ቻሉ ። ሕዝቡን በዚህ መልኩ ካረጋጉና ሥነ-ልቦናቸውን ጤናማ ማድረግ ከቻሉ በኋላ በቀጥታ ወደ ሱልጣኑ በመሄድ ተታሮችን እንዲዋጋቸውና እንዲፋለማቸው አነሳሱት ። ሱልጣኑም ምክራቸውን በአዎንታ ተቀበላቸው ። በወቅቱ ሸይኹል ኢስላም ለሹማምንቱ እና ለመሳፍንቱ ባለድል እንደሚሆኑ በአሏህ ስም እየማሉ ለጂሃድ ያነሳሷቸው ነበር ። አሚሮቹ እና ሹማምንቱ፡– ((*ሊንሻ ኣሏህ ባለድል ትሆናላችሁ ማለትም ኣሏህ ከሻ ባለድል ትሆናላችሁ*)) በሉ ቢሏቸውም እርሳቸው ግን :– ((*በምናልባት ሳይሆን በእርግጠኝነት ባለድል እንሆናለን ሊንሻ ኣሏህ !!*)) ይሉ ነበር ።

«ተታሮች ለወረራ በሚመጡ ወቅት ውጊያው የሚደረገው ምንን መሰረት ኣድርጎ ነው ?!» የሚለው ነጥብ በሰዎች ውስጥ ውዥንብር ፈጥሮ ነበር ። ምክኒያቱም « *ወራሪዎቹ ከላያቸው ሲታዩ የእስልምናን የእምነት ሥርዓት የሚያከናውኑ ሙስሊሞች ናቸው ። እነዚህን ሙስሊሞች እንዴት ነው ጂሃድ ኣውጀንባቸው የምንዋጋቸው ?!*» የሚል ኣደገኛ ብዥታ ተፈጥሮ ነበር ። ሸይኹል ኢስላም ረሒመሁሏሁ ተዓላ በአፋጣኝ የነዚህን ወራሪ ኃይሎች ማንነት ገልጸው ለሕዝቡ ማስረዳት ችለዋል ። እነዚህ ወራሪ ኃይሎች ሰሃቦች ረዲየሏሁ ዐንሁም የተጋደሏቸው ኸዋሪጆች ዓይነት እንደሆኑና ሙስሊሞች ላይ ወሰን ያለፉ ዕብሪተኞች በመሆናቸው ነው እነርሱ ላይ ጂሃድ ታውጆ ሙስሊሞች የሚፋለሟቸው ብለው ብያኔ በመስጠት በሕዝቡ ውስጥ የተሰራጨውን

ብኸጦታ በቀላሉ ከአእምሯቸው ውስጥ መጥረግ ችለዋል ። በሙሉ ብርታትና ቆራጥነት፡ –((*በአናቴ ላይ ከቡር ቁርአንን ተሸክሜ አንኳን ብሆን ፤ አኔ የተታሮችን አቋም ይዤ ወይም ደግፌ ሰራመድ ብታዩኝ አንገቴን በመቅላት ግደሉኝ !*)) ሲሉ ነበር የተናገሩት ። ይህን የማያወላውል ንግግር ሲሰሙ ሰዎች ውስጣቸው ሰከነ ። ኃይላቸውንም አንድ አድርገው ለአንድ ግብ ለመፋለም ብርታት ሰጣቸው ። በግብጽ የሚገኘው ሱልጣን ሸይኹል ኢስላም ረሒመሁሏሁ ተዓላ ከእርሱ ሠራዊት ጎን ለጂሃድ እንዲሰለፉ ሲጠይቃቸው ፡– ((*በነብያዊው ሱንና መሠረት አንድ ግለሠብ ለጂሃድ ሲወጣ ከወገኑ ሰንደቅ-አላማ ሰር ነው መሰለፍ ያለበት ። አኛ ደግም ከሻም ሠራዊት ውስጥ የምንገኝ ወታደሮች ሰለሆን በነርሱ ሰንደቅ-አላማ ሥር አንጂ አንሰለፍም !*)) ብለው ነበር የመለሱለት ።

ዘመቻው እስኪጠናቀቅ ድረስ ወታደሮቹ ፆማቸውን ፈትተው እንዲመገቡ ፈትዋ ሰጡ ። ምክኒያቱም ነፍሲያ ወደፊት በሙሉ ኃይሏ ለመዝመት እንድትበረታ የሚያደርጋት ሁነኛ መንገድ ስለሆነ ፆምን መፍታት እንደሚበልጥ ገልጸው አስረዷቸው ። ወደ መሳፍንቱም በመሄድ እያበረታቷቸው አብረዋቸውም ተቀምጠው የተወሰነ ምግብ ይመገቡ ነበር ። እንደልማዳቸው የሚመገቧትን ያችን ትንሽ መጠን ተመግበው፡ – ((*ፆምን መፍታታችሁና አንዲህ መመገባችሁ በኣጅጉ ብርቱ ያደርጋችኋል*)) ብለው በመግለጽ ነብዩ ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም መካን በድል የተቀዳጁ ወቅት ፆማቸውን ፈትተው እንደነበር ገልጸው ያስረዷቸው ነበር ። ፍልሚያው ተፋፍሞ ብርቱ የሆነ ውጊያ ከተደረገ በኋላ ተታሮችን አሸንፈው ድል ነሏቸው ። «*የሹቅሑብ ዘመቻ* » በመባል የሚታወቀው ይህ ዘመቻ ሸይኹል ኢስላም ረሒመሁሏሁ ተዓላ ታላቅ አሻረቸውን ያሳረፉበት ገድላቸው ነው ።[56]

ኢብን ዐብዲልሃዲ የጀግንነት ታሪካቸውን ሲዘክሩ፡– ((*ከሻም አሚሮች መካከል አንድ በዲኑ ጠንካራ ፣ ታማኝ ፣ሐቅን በመናገር የተመሰከረለትና በግዛቱ ውስጥ ዝናው የናኘ አሚር በፍልሚያው ወቅት የገጠመውን ሲገልጽ « ሸይኹ –ማለትም ሸይኹል*

ኢስላም ረሒመሁሏሁ ተዓላ –የፍልሚያው ዕለት ሁለቱም ሠራዊቶች መፋለም ጀምረው ሳለ እንዲህ አሉኝ ፦ "እገሌ ሆይ! ምት ካለበት ገብቼ እንድፋለም የምት ምድብ ላይ መድበኝ "አሉኝ ።» ከጠላት ፊት እንዲፋለሙ ቦታ ሰጠኋቸው ። ጠላቶች በወቅቱ ሰይፎቻቸው ከአቧራው ግርዶሾች ውሰጥ አልፈው ሲያብረቀርቁ ይታዩ ነበር ። እንደነርፍም ግር ብለው በመትመም ወደኛ እያሰገመገሙ በመሮጥ ላይ ነበሩ ። ከዚያም እኔ « አለቃዬ! ይህ አሁን የመደብኮት ቦታ የምት ምድብ ነው ። ጠላትም ከዚህ አቧራ ውሰጥ እየተንደረደረ ወጥቶ ከዚህ ቦታ የቆመውን ሰው ከመግደል ውጭ ሌላ በምሕረት አያልፋትም ። ምትን ሊጋፈጡ ይሽው እንደተመኙት ከዚህ መድቤዎታለሁ » አልኳቸው ። ከዚያም ፍሊሚያው ተጧጧፈ ፣ አቧራውም ጨሰ ፣ ጦርነቱ ጋለ በእኔና በእርሳቸውም መካከል ፍልሚያው ለያይቶን እንዳንተያይ ጋረደኝ ። አሏህ ድል አቀዳጀን ። ከፍ ባለ ድምፅ ሠራዊቱን የሚያነቃቁ እና የሚያበረታቱ ፤ ከጦር ሜዳው መሸሽ የሚያስከተለውን ፍድዳ በማስጠንቀቅ ሠራዊቱን በፍልሚያው ላይ እንዲበረቱ የሚያጸኑ የሁለት ሰዎችን ድምፅ አሰማ ነበር ። አሻግሬ ሰመለከት ሸይኹ እና ወንድማቸው ነበሩ ። » ብሎ ተረከልኝ)) ይላሉ ። [57] እኒህ ታላቅ ሰብእና በዚህ ዓይነቱ ክስተት ላይ ያስመዘገቡት ገድል ሕይወታቸውን በብዕር እና በአንደበት በማስተማር ብቻ ያልገቱ የጦር ሜዳም ጀግና እንደነበሩ ታሪካቸው ያረጋግጥልናል ።

በዕውቀት የነበራቸው ማዕረግ እና ዑለሞች ስለርሳቸው ሰብእና የሰጡት ማረጋገጫ

ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚየህ ረሒመሁሏሁ ተዓላ በዕውቀታቸው ሁሉን አቀፍ የዕውቀት ባለቤት በመሆን ታላቅ ሰብእና ለመሆን የበቁ ብርቅዬ ሰው ናቸው ። በዘመናቸው የነበሩትን ተፎካካሪዎቻቸውን በሙሉ በሁሉም መስክ አንበርክከው የአዋቂዎች አዋቂ የሊቃውንት ሁሉ መሪ የሆኑ ሊቅ እንደሆኑ ማስመስከር ችለዋል ። በእርግጥ ሰብእናቸው የተሟሏ ኢማም ፣ ሁለመናቸውን ለእስልምና የቸሩ ሸይኹል ኢስላም ፣ ኢስላማዊ መርሆችና የእምነት አመለካከት በአደገኛ ማዕበል ከመናወጥ